# “ሮመዳንን ለሠላም”

አወል አባፊጣ- ከለቡ   8/8/12

በቅርቡ በመዲናችን አዲስ አበባ “ጥያቄያችን ሃይማኖታዊ ነው” በሚል ለአመፅና ለብጥብጥ ወደጎዳና የወጡ ወገኖች እንደነበሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። እነዚህ ወገኖች በተለይም በአወሊያና በታላቁ አንዋር መስጂድ አካባቢዎች ባካሄዷቸው ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ምንም እንኳን የህይወት መጥፋት አደጋ ባይከተልም ቀላል የማይባል ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት ግን ደርሷል። ሰላምን ለማስጠበቅ በስፍራዉ የተሰማሩ የፖሊስ አባላት ሳይቀሩ ለጉዳት መጋለጣቸው በወቅቱ የሰማነው ክስተት ነው።

ሁከቱ ተጨማሪ ጉዳት ሳያስከትልና ሳይስፋፋ በአጭሩ የተቀጨ ቢሆንም፤ ክስተቱን ተከትሎ ከተለያዩ ወገኖች የሚሰነዘሩ አስተያየቶችና መላ-ምቶች በስፋት ሲደመጡ ሰንብተዋል ። የአመፁ ተዋንያን ናቸው ተብለው ከተፈረጁት ጥቂት ግለሰቦች ጀምሮ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ስለሁኔታው ከየራሳቸው ፍላጎት በመነሳት አስተያየት የሰጡ ሲሆን፤ በመንግስት በኩልም የተሰጠ ማብራሪያ ነበር። ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በሰላም ወዳዱ ህብረተሰብ ዘንድ እነዚህን ወገኖች አስመልክቶ በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄዱ የተቃውሞ ሰልፎችም እንደቀጠሉ ናቸው።

ታዲያ እዚህ ላይ ‘የብጥብጡ መንስኤ ምንድነው? ሁከት ፈጣሪዎቹ እነማን ናቸው? ጥያቄው እውነት ኃይማኖታዊ ይዘት ነበረው ወይስ ሌላ ድብቅ አጀንዳ አለው? ሁኔታው በአሁኑ ወቅት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?’ የሚሉ ጥያቀዌዎችን ማንሳት ተገቢ ነው። እናም በዛሬው ፅሁፌ  እነዚህን ጥያቄዎች በዋነኛነት በማንሳት ለማብራራት እሞክራለሁ።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የአንድ አሊያም የጥቂት እምነት ተከታዮች ሀገር አይደለችም። ማንም ዜጋ የፈለገውን ኃይማኖት በእኩልነትና በነፃነት የማምለክ ህገ - መንግስታዊ ዋስትና ተሰጥቶታል። በመሆኑም ማንም ዜጋ በአምልኮቱ የተነሳ የሚደርስበት ተፅዕኖ የለም። አንዱ ኃይማኖት የሌላውን በማንቋሸሽ፣ በመቃወም አሊያም ከሌሎች እኩይ ዓላማዎች ተነስቶ ተፅእኖ ለማሳረፍ፣ ለማበጣበጥ፣ ለማሳደድና መሰል ተግባራት ለመፈፀም አይችልም። ይህን መሰሉ ድርጊት በታሪካችን የማይታወቅ መሆኑ እሙን ነው። ሀገራችን ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ከምትታወቅባቸው መልካም እሴቶቿ ውስጥ አንዱ ጉዳይ በርካታ ሃይማኖቶች ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩባት መሆኗ ነው።

በኢፌደዴሪ ህገ - መንግስት በግልፅ እንደተደነገገው፤ መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው። መንግስት በማንኛውም ሃይማኖታዊ ስርዓት ውስጥ እጁን አስገብቶ “እንዲህ መደረግ አለበት፤ ይህ ደግሞ መከናወን የለበትም…” እያለ የሚወስንበት ነገር አይኖርም። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ትልቁ ጉዳይ ቢኖር፤ መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ ናቸው በሚባልበት ወቅት የእምነት ተቋማት አሊያም ተከታዮች በሃይማኖት ሽፋን የሃገሪቱን ህግ  የሚጥስ ተግባር መፈፀም ይችላሉ ማለት አይደለም።

በመሆኑም የኃይማኖት ተቋማትም ሆኑ ተከታዮቻቸው ኃይማኖታዊ ስርዓታቸውን ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መልኩ መፈፀም ይኖርባቸዋል። ጥያቄ ቢኖራቸው እንኳን ህግና ስርዓትን ተከትለው ማቅረብ ብቻ ነው የሚገባቸው እንጂ፣ ጥያቄው ሃይማኖታዊ ቢሆን እንኳን ለአመፅና ለብጥብጥ መጋበዝ ሕገወጥ ነው።

በመሰረቱም የትኛውም ሃይማኖት ሰላምን እንጂ ሁከትን የሚፈቅድ አለመሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በማንኛውም ሁኔታ ለአመፅና ለግርግር የሚነሳሳ ኃይል ከተፈጠረ ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ሳይሆን የሀገርንና የሕዝብን ሰላም የማወክ እንቅስቃሴ መሆኑ እርግጥ ነው። ታዲያ መንግስትም ቢሆን ይህን መሰሉን ተግባር እያየ በዝምታ ሊያልፍ አይችልም። የሀገርን ሰላም የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ሁኔታውን ፈር የማስያዝ ግዴታ አለበትና።

ለመሆኑ በሀገራችን የኃይማኖት ነፃነትና እኩልነት በተግባር ተፈፃሚ እየሆነ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ በቅርቡ በሃይማኖት ሽፋን የተቃጣው የአመፅ እንቅስቃሴ ከቶ ከምን የመነጨ ነው?– መነሳት ያለበት ወቅታዊ ጥያቄ ነው።

ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያስችል ዘንድ “ወሐቢያ” በሚል በሃይማኖት ሽፋን የተደራጀውን ሃይል የኋላ አመጣጥን በጥቂቱም ቢሆን መመልከት ያስፈልጋል። እንደሚታወቀው የእስልምና ኃይማኖት በሃገራችን የነበረ፣ ያለና ለወደፊትም የሚኖር ነው። የኃይማኖቱ ተከታዮችም ቢሆኑ እርስ በርሳቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከሌሎች እምነት ተከታይ ወንድሞቻቸው ጋር ተከባብረውና ተቻችለው ለዘመናት ኖረዋል፤ወደፊትም አብረው ይኖራሉ።

ይህ እውነታ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን ለዚህ ክስተት መንስኤ የሆኑ ቡድኖች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ማቆጥቆጣቸው አልቀረም። እነዚህ ቡድኖች ሲነሱ ሃይማኖታዊ አላማን የሰነቁ መስለው ቢሆንም፤ ከዚህ በስተጀርባ ግን ሌላ አጀንዳ የማራመድ ዕቅድ ነበራቸው። ይሁንና በሃይማኖት ሽፋን ለማራመድ ያሰቡትን ሴራ ገሃድ እስካላወጡና ሌላ ጉዳት እስካላስከተሉ ድረስ ማንም እውቅና ሊነፍጋቸው አይችልም። ምክንያቱም በሰላማዊ መንገድ ሃይማኖታዊ ስርአታቸውን የማካሄድ ህገ መንግስታዊ መብትና ነፃነት ያላቸው ስለሆነ ያለምንም ተፅእኖ ለመደራጀት ችለዋል፤ ለጥቂት ጊዜያትም ቢሆን ሰላማዊ መስለው ለመታየት ሞክረውም ነበር። በመሰረቱ ምንም ይሁን ምን የራሳችንን እምነት ይዘን በሰላማዊ መንገድና የሌሎችን መብት ሳንነካ ሃይማኖያዊ ሥርዓታችንን ጠብቀን እንንዛለን ማለት በራሱ ስህተት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ችግሩ የሚመጣው የሌሎችን መብትና ነጻነት፤ባህልና እምነት ወዘተ በመደፍጠጥ የራስን የበላይነት በሌሎች ላይ በኃይል ለመጫንና ከሁሉም በላይ በዚህ ከለላ ድብቅ ፖለቲካዊ ዓላማን ለማሳካት ሲባል ሕግን በመተላለፍ በአመጽና በሁከት የህብረተሰቡንና የአገርን ሰላም ለማወክ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲገባ ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ድብቁን አጀንዳቸውን ሸሽገው መቆየታቸው ከጀርባቸው ሆነው “በዚህ ግቡ፤ በዚህ ውጡ” እያሉ እንዳሻቸው ከሚያሽከረክሯቸው የውጭ አክራሪ ቡድኖች የሚያገኙትን ድጋፍ የሚያሳጣቸውና

ወደመጥፋት የሚያሸጋግራቸው መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ውስጥ ውስጡንም ቢሆን እኩይ ተግባራቸውን መፈፀም ነበረባቸውና እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉ። እናም ይህንን የአመፃ ርምጃቸውን ለዘመናት በፍቅርና በአንድነት በኖረው የሙስሊሙ ህዝብ ላይ ነበር በቅድሚያ መተግበር  የጀመሩት።

እነዚህ ኃይሎች የተደራጁበት ዓላማ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ገና በለጋ የሁከት ዕድሜያቸው በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ በሚያራምዱት አፍራሽ ተግባር አረጋግጠዋል። ለዚህም የሙስሊሙ ማህበረሰብ አኩሪ እሴቶችን ለማጥፋት ያደረጉት ርብርብ አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው። የእምነቱ ተከታዮች ለድሃ የሚመፀውቱት የ'ሰደቃ' ስርዓት እንዳይፈፀም፣ የመቃብር ስፍራዎችን በማፍረስ ሙስሊሞች ኃይማኖታዊ ስርዓታቸውን ጠብቀው እንዳይቀበሩ በመከልከል፣ የሃይማኖቱ መሪዎችን/ኢማሞችን/ በማሳደድና በመግደል፣ …ወዘተርፈ ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች የእምነቱን እሴቶች ለማጥፋት ካካሄዷቸው ዘመቻዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ፍቅርና አንድነት እንዳይኖር ያካሄዷቸው ዘመቻዎች እንደነበሩም የሚካድ አይደለም። በሰበብ አስባቡ ሙስሊሙ ህዝብ እርስ በርሱ እንዲበጣበጥ፣ ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወንድሞቹ ጋርም አብሮ ተከባብሮና ተቻችሎ እንዳይኖር አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ጥረዋል፤ግረዋል። ያለአንዳች ምክንያት  የሙስሊሙን ሕዝብ  "ለጅሃድ ጦርነት ተነስ" እያሉ ሲሰብኩ መኖራቸውም ከማንም የተሰወረ ሃቅ አይደለም።

ይሁንና የእነዚህ ሃይሎች ፍላጎት ፈፅሞ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ከሰላማዊው የእምነቱ ተከታይ የተሰወረ አልነበረም። በመሆኑም ህዝበ- ሙስሊሙ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፤ የሚሰብከውን የቡድኑን የዘወትር ውትወታ ሊቀበለው አልቻለም። እናም ነገረ-ስራው በትክክለኛ ሃይማኖታዊ መሰረት ላይ የተገነባ ባለመሆኑ በሙስሊሙ ማህበረሰብ  ዘንድ ተቀባይነት አጥቷል። ግና እነዚህ ኃይሎች ፍላጎታቸው ሌላ ነበርና ከተያያዙት አፍራሽ ተልዕኮ ሊታቀቡና ወደ ትክክለኛው ጎዳና ሊመለሱ አልቻሉም። ይልቁንም ተቀባይነት ማጣታቸው ይበልጥ ተስፋ እያስቆረጣቸውና እንቅስቃሴያቸውም ሃይል የተሞላበት ሆኖ ነው የቀጠለው።

እነዚህ ሃይሎች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ የጀመሩትን አፍራሽ እንቅስቃሴ በመያዝ ከመንግስት ጋርም ለመጋፈጥ ጥረት ከማድረግ ወደኋላ አላሉም።  "ጥያቄ አለን፤ ተገቢው ምላሽ ይሰጠን" በሚል ከመንግስት ጋር ተደጋጋሚ ሙግት ሲገጥሙ ቆይተዋል። ይህን በሚያደርጉበት ወቅት ግን ከመንግስት በኩል የገጠማቸው እንዳሰቡት የ"እንካ ሰላንቲያ" አይነት ሳይሆን ሁኔታውን በእርጋታ እና በሰከነ መንገድ በመያዝ መፍትሔ የመሻት ጉዳይ ነበር። ይህ የሆነው ደግሞ የእነዚህ ሃይሎች ዓላማ ምን እንደሆነ መንግስት ሳይረዳው በመቅረቱ አይደለም– ለጥያቄዎቹ ቅድሚያ በመስጠቱ እንጂ። እናም ቀደም ሲል በቡድኑ ቀርበው የነበሩት ሦስት ጥያቄዎችን በተገቢው አዳምጦ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ችሏል።

ይሁንና ለቀረቡት ጥያቄዎች መንግስት ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል ሲባል ቡድኑ ባገኘው ይሁንታ ረክቷል ወይም እጁን ሰብስቦ ተቀምጧል ማለት እንዳልሆነ ውድ አንባቢዎቼ ልብ ሊሉት ይገባል። ቡድኑ ላቀረባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ያግኝም፣ አያግኝም ምንም የሚደንቀው ጉዳይ አልነበረም። እንዲያውም ጥያቄዎቹ ሊመለሱ ባይችሉ ኖሮ፤ በሰበቡ ብጥብጥ ለማስነሳት እንደመልካም አጋጣሚ ለመጠቀም ፍላጎት ነበረው። ዳሩ ግን እንደገመተው ሳይሆን በመቅረቱ ለሌላ ተደራራቢ የፖለቲካ ጥያቄዎችና የኃይል እርምጃዎች ራሱን ማዘጋጀቱን ሊገፋበት ችሏል።

እነዚህ ሃይሎች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ሲያደርሱ የቆዩትም ሆኑ ለመንግስት ሲያቀርቡ የነበሯቸው መቋጫ ያልነበራቸው የፖለቲካ ጥያቄዎች በዚህች ሀገር ላይ ፅንፈኝነትንና አክራሪነትን ለማስፋፋት ቆርጠው የተነሱ መሆናቸውን በገሃድ ያረጋገጡበት ነው ማለት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ግን ሴራቸው ቀድሞ ቢታወቅም መንግስት 'ምናልባትም እነዚህ ወገኖች ከስህተታቸው ይታረማሉ' ሆደ ሰፊነት እርምጃ ሊወስድባቸው አልፈለገም። እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስም በሙስሊሙ ህዝብም ይሁን መንግስት በኩል ታላቅ ትዕግስትና ብስለት የተሞላበት አካሄድ ተስተውሎ ቆይቷል።

ይሁን እና ቡድኑ በማንኛውም መልኩ የሚያደርጋቸው የብጥብጥ ግፊቶች መንግስትም ሆነ ህዝበ ሙስሊሙ በተከተሏቸው የሰከኑ አካሄዶች እየተቀለበሱ መቀጠላቸው አልተዋጠለትም። ሃቁን ተገንዝቦ አካሄዱን ከመቀየር ይልቅ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። በነገራችን ላይ የዚህ ቡድን የተስፋ ቆራጭነት ጉዞ ጥቂት ቁጥር ላላቸው ተከታዮቹ ብቻ ሳይሆን፤ ኃይሉን በስውር በመደገፍ ሀገራችን ውስጥ ሁከት እንዲነግስ ፍላጎት ላላቸው የውጭ ፅንፈኛ ሃይሎችም ብርቱ ህመም ሆኗል። በመሆኑም እነዚህ ኃይሎች በይማኖት ስም የለበሱትን ካባ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውልቀው ስውር ፍላጎታቸውን አደባባይ ለማውጣት ወደ ተገደዱበት ደረጃ ለመሸጋገር በቅተዋል።

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከርኩት እነዚህ ሃይሎች በእስልምና ስም መነገድን በተያያዙበት ወቅት ሙስሊሙ ማህበረሰብ የ"ሰደቃ" ስርዓቱን እንዳያከናውን ለማስገደድ ብርቱ ጥረት አድርገዋል።ይሁን እንጂ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተነጠሉና እርቃናቸውን በቀሩበት ወቅት ሲያወግዙትና ሊያጠፉት ጥረት ሲያደርጉ ወደ ነበረው ሃይማኖታዊ ስርአት ለመመለስ ነው የተገደዱት።

ለዚህም በቅርቡ ለብጥብጥ ራሳቸውን ሲያዘጋጁ ሰደቃ በማድረግ "አንድነት" በሚል በአወሊያ አከናውነውት የነበረው ዝግጅት ቡድኑ ከመነጠሉ የተነሳ ወደ ከፋ ተስፋ መቁረጥ የተሸጋገረ መሆኑን በገሃድ የሚያረጋግጥ ዕውነታ ነው። "አንድነት" በሚል ያዘጋጁት ስብሰባ ደግሞ ቡድኑ ከሙስሊሙ ህዝብ ልዩነት አለኝ በሚል የተነጠለና ለአመታትም አንድ አለመሆኑን ተቀብሎ ሲንቀሳቀስ የቆየ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ግና ቡድኑ አብሮት ድንጋይ የሚያወራውረውን ደጋፊ ለማሰባሰብ አንድነቱ ድንገት ቢታወሰውም ቅሉ፤ ስለ ሰላም የሚሰብከውን እስልምና ተጋፍቶ ለወጣው ይህ ፅንፈኛ ኃይል "አንድ" መሆኑን ያረጋገጠለት ምዕመን አልተገኘም።

ታዲያ ሁኔታው በዚህ ቀጥሎ የቡድኑ አጀንዳ ሃይማኖታዊ ሳይሆን ዓይን ያወጣ ፖለቲካ መሆኑ በአደባባይ እርቃኑን መታየቱ አይቀሬ ሆኗል። ግና እንዴት?–እውነታው እንዲህ የሚነበብ ነው። …እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የሀገራችን ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መዲናም ናት። በየጊዜው ታላላቅ ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎችን ታስተናግዳለች። በቅርቡም የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባን ማስተናገዱ ይታወሳል።

ታዲያ በዚህ ወቅት እነዚህ ሃይሎች የሀገርንና የህዝብን ሰላም ለማደፍረስ ብሎም በእንግዳ ተቀባይነትና በሰላምና ፀጥታ በኩል ህዝባችን የገነባውን መልካም ስም ለማደብዘዝ ያለመ የነውጥ እንቅስቃሴ ለማካሄድ ነበር ቆርጠው የተነሱት። ለዚህም ደግሞ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ አባላቶቻቸውን “ስብሰባ እናካሄዳለን” በሚል ስም የጠሩበት ሁኔታ ነበር። ቡድኑ ብጥብጥ እንዲያካሄድም በድብቅ ድጋፍ ያደርጉለት ከነበሩ አንዳንድ የውጭ ሃይሎች ስፖንሰር የተደረገ ለመሆኑ ውስጠ አዋቂዎች ይፋ ያወጡት የአደባባይ ሚስጢር ነው።

ይሁንና በዚህ መልኩ የተነሱት ነውጠኞች የአመፅ እንቅስቃሴያቸውን ባሰቡት መልኩ ሊያካሄዱት አልቻሉም። በአፍሪካ መሪዎች የስብሰባ መጀመሪያ ዋዜማ ላይ በአወሊያ አካባቢ ለማስነሳት ያሰቡት ሁከት በተለይም ከሰላማዊው የሙስሊም ማህበረሰብ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። የፈጠሩት ግርግርም ሊከሽፍ የቻለው በዋነኛነት በአካባቢው የነበረው ህዝበ-ሙስሊም “ሃይማኖታችን የፅንፈኞች መጠቀሚያ ሊሆን አይችልም” ብለው በመረባረባቸው ነበር። የፀጥታ ሃይሎችም ያለአንዳች የኃይል እርምጃ ብልሃት በተሞላበት እንቅስቃሴያቸው ብቻ ሁኔታውን በቀላሉ ለማክሸፍ ችለዋል።

እርግጥ አክራሪዎቹ በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ወቅት የከሸፈባቸውን የሁከት እንቅስቃሴ  በታላቁ የሮመዳን ፆም መግቢያ ወቅት ለመድገም ነበር የተረባረቡት። በወቅቱ ዋነኛ ግባቸው በታላቁ አንዋር መስጂድ ላይ አድርገው የነበረ ሲሆን፤ በመርካቶ አካባቢም ትርምስን ፈጥረዋል። ወደ ታላቁ አንዋር መስጂድ በሃይል ገብተው ለፀሎት የተሰባሰበውን ህዝብ አግተዋል፣ ሃይማኖታዊ ስርአቱን ከማወካቸውም ባሻገር ስርአቱን የሚመሩ የተከበሩ ኢማሞችን ደብድበዋል፣ ድምፅ ማጉያዎችንና ጄኔረተሮችን ተቆልፈውባቸው ከሚገኙ ክፍሎች ሰብረው በማውጣት የጅሃድ ጦርነት ቅስቀሳ አካሂደዋል፤ ጥሪያቸውን ባወገዘ ላይም ዛቻንና ድብደባን ሰንዝረዋል።

በአጠቃላይ ይህ በሃይማኖት ሽፋን ለማካሄድ የታሰበው የፅንፈኝነት እንቅስቃሴ አራማጆችም በሙስሊሙ ህዝብ የተጠሉና የተወገዙ መሆናቸውን አውቀው እጃቸውን ሰብስበው ለመቀመጥ የተገደዱበት ሁኔታ እየታዬ ነው። እናም ሙስሊሙ ህዝባችን እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በፅንፈኞች ሴራ ሳይዘናጋ የጀመረውን የታላቁን ሮመዳን ፆም በፍፁም ሰላምና ደስታ ቀጥሏል። “ሮመዳንን ለሰላም” በማለትም ሃይማኖታዊ ፆሙን አስደሳች በሆነ መንፈስ ተያይዞታል–ዛሬም የእክራሪዎችን ጩኸት ወደ ጎን በማለት። ሮመዳን ከሪም!!